በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን።

# ርዕስ፡- ሐሰተኛ ተአምራት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

ጥር ፲፫ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# *መግለጫ*

## ሐሰተኛ ተአምራት ወይም የተአምራቱ አድራጊዎች የምንላቸው እነማን ናቸው?

- *ሙታን ሳቢ፡-* ከሙታን መናፍስት መነጋገር የሚችሉ
- *አስማተኛ ወይም ሞራ ገላጭ፡-* ወደፊት ስለሚሆነው የሚናገሩ' ኮከብ ቆጣሪዎች
- *ጠንቋዮች፡-* በተለያዩ መንገዶች የሚጠነቁሉ
- *ሙዋርተኛ፡* ወደፊት መልካም ወይም መጥፎ ይሆናል ብለው ምልክት የሚያሳዩና በዚሁ ላይ የተመሰረተ የሕልም ፍቺ የሚሰጡ
- *በድግምት የሚጠነቁሉ፡* የተለያዩ የአጋንንት ኅቡእ ስሞችን በማካተት የተጻፉ ጽሑፎችን በመጻፍ ወይም በማንበብ የሚጠነቁሉ (መስተፋቅር' መድፍነ ጸር...)
- *መናፍስት ጠሪዎች፡* አጋንንትን የሚጠሩ' ጋኔን የሚሳትቱ
- *መተተኞች፡* የተለያዩ ነገሮችን በመጠቅለል ወይም ቆፍሮ በመቅበር የሚመትቱ

የነዚህ መነሻ ምንጩ ማነው?

1. ሳጥናኤል
2. አሕዛብ (የጥንት ግብጻውያን' ግሪካውያን' ባቢሎናውያን' የፋርስ ሰዎች' ወዘተ...)

# መግለጫ

- ከላይ በተጠቀሰው መንገድ የሚሰሩ ተአምራት ጎጂ ብቻ ሳይሆኑ ሐሰትም ናቸው፡፡
  - ተአምራቱ ፍጹም አይደሉም ሁሉንም ዓይነት ያለችግር ማሳመን ወይም ማሸነፍ አይችሉም፡፡
  - ፈውሱ ሥጋዊ እንጂ መንፈሳዊ አይደለም፡፡ ማቴ 16 ፤ 26
  - ለዚህ ዓይነት ፈውስ ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች ሳይፈልጉ ይዘፍናሉ፤ ይደንሳሉ፤ ወዘተ. ይህም ሰይጣናዊ ሥራ ለመሆኑ ማሳያ ነው፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለፈውስ የመጣ ሰው በላዩ የሰለጠነበትን ኃይል አቅም እንዳይኖረው በማድረግ ቤ/ክ በእግዚአብሔር ስም ታስታግሰዋለች እንጂ ኃይሉ ከእግዚአብሔር በላይ የሆነ ያህል ሲወራች ማዳነቂያ አድርጋ አቅርባ አታውቅም፡፡
  - ሰይጣን የብርሃን መልአክም መምሰል ስለሚችል ቅዱሳኑን እየመሰለ እውነተኛ ባልሆኑ ተአምራት ሊያምታታ እንደሚችልም ማስተዋል አለብን፡፡ 1ኛ ቆሮ 11 ፤ 14

# መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

1. “መተተኛይቱን በሕይወት እንድትኖር አትፍቀድላት።” ዘጸአት 22 ፥ 16

2. “ከደሙ ጋር ምንም አትብሉ አስማትም አታድርጉ፥ ሞራ ገላጭም አትሁኑ።” ዘሌዋ 19 ፥ 26

3. “ወደ መናፍስት ጠሪዎችና ወደ ጠንቋዮች አትሂዱ እንዳትረከሱባቸውም አትፈልጉአቸው እኔ እግዚአብሐር አምላካችሁ ነኝ።” ዘሌዋ 19 ፥ 31

4. “መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችንም በሚከተል፥ በሥራቸውም በሚያመነዝር፥ በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብዳለሁ፥ ከሕዝቡም መካከል ለይቼ አጠፋዋለሁ።” ዘሌዋ 20 ፥ 6

5. “ሰው ወይም ሴት መናፍስትን ቢጠሩ ወይም ጠንቋዮች ቢሆኑ ፈጽመው ይገደሉ በድንጋይ ይውገሩአቸው ደማቸው በላያቸው ነው።” ዘሌዋ 20 ፥ 27

6. “አምላክህ እግዚአብሔር ወደሚሰጥህ ምድር በገባህ ጊዜ እነዚያ አሕዛብ የሚያደርጉትን ርኵሰት ታደርግ ዘንድ አትማር። ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፥ ምዋርተኛም፥ ሞራ ገላጭም፥ አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቍልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው ስለዚህም ርኵሰት አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ ያሳድዳቸዋል። አንተ ግን በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ሁን። የምትወርሳቸው እነዚህ አሕዛብ ሞራ ገላጮችንና ምዋርተኞችን ያዳምጣሉ አንተ ግን እንዲሁ ታደርግ ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር ከልክሎሃል።” ዘዳግ 18 ፥ 9-14

# መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?...

7. ❋እርሱም፡- የሚጮኹትንና ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው የሚናገሩትን መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ጠይቁ ባሉአችሁ ጊዜ፥ ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባውምን? ወይስ ለሕያዋን ሲሉ ሙታንን ይጠይቃሉን?፤ ኢሳይያስ 8 ٭ 19

8. ❋እናንተ ግን። ለባቢሎን ንጉሥ አትገዙም የሚሉአችሁን ነቢያቶቻችሁንና ምዋርተኞቻችሁን፥ ሕልም አላሚዎቻችሁንና ቃላተኞቻችሁን መተተኞቻችሁንም አትስሙ።፤ ኤርምያስ 27 ٭ 9

9. ❋የእስራኤልም አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። በመካከላችሁ ያሉት ነቢያቶቻችሁና ምዋርተኞቻችሁ አያታልሉአችሁ፥ እናንተም የምታልሙትን ሕልም አትስሙ።።፤ ኤርምያስ 29 ٭ 8

10. ❋መተትንም ከእጅህ አጠፋለሁ፥ ምዋርተኞችም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆኑልህም።፤ ሚክ 5 ٭ 12

11. ❋ስለ መግደላቸውም ቢሆን ወይም ስለ አስማታቸው ወይም ስለ ዝሙታቸው ወይም ስለ ስርቆታቸው ንስሐ አልገቡም።።፤ ራእይ 9 ٭ 21

12. ❋ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኞዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።።፤ ራእይ 21 ٭ 8

# መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?...

13. *ውሻዎችና አስማተኞች ሴሰኞዎችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትንም የሚያመልኩት ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ።፤ ራእይ 22 ፥ 15

14. *ሳሙኤል ግን ሞቶ ነበር፥ እስራኤልም ሁሉ አልቅሰውለት ነበር፥ በከተማውም በአርማቴም ቀብረውት ነበር። ሳኦልም መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ከምድር አጥፍቶ ነበር። ፍልስጥኤማውያንም ተሰብስበው መጡ በሱነምም ሰፈሩ ሳኦልም እስራኤልን ሁሉ ሰበሰበ፥ በጊልቦዓም ሰፈሩ። ሳኦልም የፍልስጥኤማውያንን ጭፍራ ባየ ጊዜ ፈራ፥ ልቡም እጅግ ተንቀጠቀጠ። ሳኦልም እግዚአብሔርን ጠየቀ እግዚአብሔርም በሕልም ወይም በኡሪም ወይም በነቢያት አልመለሰለትም። ሳኦልም ባሪያዎቹን፦ ወደ እርስዋ ሄጄ እጠይቅ ዘንድ መናፍስትን የምትጠራ ሴት ፈልጉልኝ አላቸው ባሪያዎቹም። እነሆ፥ መናፍስትን የምትጠራ አንዲት ሴት በዓይንዶር አለች አሉት። ሳኦልም መልኩን ለውጦ ሌላ ልብስም ለብሶ ሄደ፥ ሁለትም ሰዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ፥ በሌሊትም ወደ ሴቲቱ መጡ። እርሱም፦ እባክሽ፥ በመናፍስት አምዋርቺልኝ፥ የምልሽንም አስነሽልኝ አላት። ሴቲቱም። እነሆ፥ መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ከምድር እንዳጠፋ ሳኦል ያደረገውን ታውቃለህ ስለ ምን እኔን ለማስገደል ወጥመድ ለነፍሴ ታደርጋለህ? አለችው። ሳኦልም። ሕያው እግዚአብሔርን! በዚህ ነገር ቅጣት አያገኝሽም ብሎ በእግዚአብሔር ማለላት። ሴቲቱም። ማንን ላስነሣልህ? አለች...በዚያም ሌሊት ሄዱ። ።፤ ቀዳ. ሳሙ 28፥3-25

15. *... ልጁንም በእሳት አሳለፈ፥ ሞራ ገላጭም ሆነ፥ አስማትም አደረገ፥ መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችንም ሰበሰበ ያስቈጣውም ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ክፉ ነገር አደረገ።... ፤ ካልዕ ነገሥት 21 ፥ 1 - 11

# ዘመናዊ ገጽታው

- በርካታ ሰዎች በምኖርበት ክፍለ ዘመን በጥንቆላ ተጠቃሚ የመሆን ሙከራ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መገኘት ደግሞ ኃጢአት ነው፡፡

- እነዚህን መንገዶች ሰይጣን ሰዎችን ከእግዚአብሔር ለማራቅ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ በስፋት ከሚታዩት ጥቂቶቹም፡-

1. ኮከብ ቆጠራ፡- መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ መጠቀም የሌለብን መሆኑን በማመልከት ግልጽ አቋሙን ይገልጻል፡፡ ኤር. 10 ፡ 2 ' ኤር. 27 ፡ 9-10 ' ዳን. 2 ፡1-4 ' ዳን. 4 ፡ 7 ' ዳን. 5 ፡ 7-9 ' ዘዳግም 4 ፡ 19' ዘዳግም 17፡ 2-5' ካልዕ ነገ. 21 ፡3-5' ሶፎንያስ 1 ፡ 5' ኢዮብ 31፡26-28' ኤርምያስ 8 ፡ 1-2

❖... በምክርሽ ብዛት ደክመሻል አሁንም የሰማይን ከዋክብት የሚቈጥሩ፥ ከዋክብትንም የሚመለከቱ፥ በየመባቻውም የሚመጣውን ነገር የሚናገሩ ተነሥተው ከሚመጣብሽ ነገር ያድኑሽ። እነሆ፥ እንደ እብቅ ይሆናሉ፥ እሳትም ያቃጥላቸዋል ሰውነታቸውንም ከነበልባል ኃይል አያድኑም እርሱም ሰው እንደሚሞቀው ፍም፥ ወይም በፊቱ ሰው እንደሚቀመጥበት እሳት ያለ አይደለም።...፤ ኢሳይያስ 47 ፡ 10 - 14

❖ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞችም የአስማተኞችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።።፤ ራእይ 21 ፡ 8

2. ጥንቆላ' ምዋርት' መተት' አስማት፡- መጽሐፍ ቅዱስ በዚህም ቢሆን መጠቀም የሌለብን መሆኑን በማመልከት አቋሙን ይገልጻል፡፡ ዘዳግም 18 ፡ 10 - 12

# <u>*ዘመናዊ ገጽታው...*</u>

- የጥንቆላን መንገድ መከተል መጨረሻው ከእግዚአብሔር መራቅና ውድቀት ነው፡፡
  - ንግሥት ኤልዛቤል መተት በመከተልዋ የተነሳ ለራስዋና ለእስራኤል የመከራ ምንጭ ሆናለች፡፡ <u>ካልዕ ነገ. 9 ★ 22</u>
- ይህን መንገድ መጠቀምን የሚያበረታቱ በርካታ መጻሕፍት ተጽፈዋል‘ በሁሉም ዕድሜ የሚገኙ ሰዎችንም ለመሳብ ፊልሞች ተሠርተዋል' መንፈሳውያንንም ለመሳብ መንፈሳዊ የሚመስሉ ሽፈኖች እየተደረጉ አገልግሎት ላይ ውለዋል' በስፋት እንደ ሥራ መስክ ተቆጥረው መተዳደሪያም ሆነው በመታየት ላይ ይገኛሉ፡፡
  - ❋ወደ ጸሎት ስፍራም ስንሄድ፥ የምዋርተኝነት መንፈስ የነበረባት ለጌቶችዋም እየጠነቈለች ብዙ ትርፍ ታመጣ የነበረች አንዲት ገረድ አገኘችን።፤ <u>የሐዋ. ሥራ 16 ★ 16</u>
- በጥንቷ ኤፌሶን ዜጎች የነበሩ ብዙዎች ጥንቆላን ይለማመዱ ነበር፡፡ ከእነርሱም መካከል ወደ ክርስትና ሕይወት የገቡት የቀድሞው ሥራቸው ሞኝነት የነበረበት የጥፋት ሥራ እንደሆነ በመረዳት መጻሕፍቶቻቸውንም ሳይቀር አቃጥለው ነበር፡፡
  - ❋ከአስማተኞችም ብዙዎቹ መጽሐፋቸውን ሰብስበው በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት፤ ዋጋውም ቢታሰብ አምሳ ሺህ ብር ሆኖ ተገኘ።፤ <u>የሐዋ. ሥራ 19 ★ 19</u>
- ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ የጥፋት ሕይወት ከሚኖሩት መካከል ከአንዱ ጋር የነበረው ግኑኝነት ምን ይመስል እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ገልጦታል፡፡
  - ❋ጳውሎስ የተባለው ሳውል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኵር ብሎ ሲመለከተው። አንተ ተንኰል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ፥ የዲያብሎስ ልጅ፥ የጽድቅም ሁሉ ጠላት፥ የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን? አሁንም፥ እነሆ፥ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት፥ ዕውርም ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም አለው። ያን ጊዜም ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት፥ በእጁም የሚመራውን እየዞረ ፈለገ።።፤ <u>የሐዋ. ሥራ 13 ★ 9 -11</u>

# ዘመናዊ ገጽታው...

- ❋ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ምንም ምን ሳያዩ የገዛ መንፈሳቸውን ለሚከተሉ ለሰነፎች ነቢያት ወዮላቸው!።፤ ሕዝቅኤል 13 ፥ 3
- ሕይወታችንን ለመምራት በጥንቆላ' ምዋርት' መተት' አስማት የምንጠቀም ልንሆን አይገባንም፡፡
  - ❋ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፥ ምዋርተኛም፥ ሞራ ገላጭም፥ አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቍልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው ስለዚህም ርኵሰት አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ ያሳድዳቸዋል። ።፤ ዘዳግም 18 ፥ 10 - 12
- በዚህ በመጨረሻው ዘመን ጥንቆላ' ምዋርት' መተት' አስማት...
  - በርካታ መጻሕፍት ተጽፈውለታል፡፡ (“The book of shadows”, “A witch’s bible”, and “The complete idiot’s guide to Wicca and witchcraft”, etc)
  - ፊልሞች ተሰርተውለታል፡፡ (“Harry Potter”, “Power Rangers”፣ "Charmed“, "The Omen“, etc)
  - ቀን ተመድቦለት ይከበራል፡፡ (“Halloween”, etc)
  - የቤተ ክርስቲያንንም ምልክቶችና ስምም በመጠቀም ሳይታወቁ ብዙዎችን በመጉዳት ላይ የሚገኙ አሉ፡፡ (በጠበል ስም የቤ/ክ ባልሆኑ መንገዶች የሚፈጸሙ አንዳንድ ጉዳቶች' መስተፋቅር' አንደ ርቢ ' የተለያዩ በአንገት የሚታሰሩ የአስማት ጽሁፎች' የተመተተበትና የተመረዘ መጠጥ ማጠጣትና ምግብ መመገብ' ወዘተ...)

# *<u>በዚህ የተዘፈቁትን እንዴት እናውቃቸዋለን?</u>*

1. *<u>ከቤተ ክርስቲያን በመራቃቸው፡-</u>* ከቤ/ክ ምስጢራት' ከቃለ እግዚአብሔር እና በቤ/ክ ከሚጠበቅባቸው ተሳትፎ ይለያሉ፡፡ በተጨማሪም ከማይታወቁ ወይም ድብቅ ከሆኑ ቡድኖች ጋር የመገናኘት አማራጮችን በመፈለግ ይጠቀማሉ፡፡
2. *<u>በኢንተርኔት ድራረ ገጽ፡-</u>* የኢሜይል ዜናዎችና ድራረ ገጾች ላይ' ተጠርጣሪ በሆኑ የመወያያ የመነጋገሪያ ክፍሎች ውስጥ መገኘት' አስቸኳይ የመልዕክት መለዋዋጫዎች ውስጥ ቀዳሚ ሆኖ መገኘት' ወዘተ...
3. *<u>በአለባበሳቸውና አቀራረባቸው፡-</u>* ጥቁር ቀለምና ሰይጣናዊ (ክፉ ምስሎችና ምልክቶች) ያሉባቸውን ልብሶች ያዘወትራሉ፡፡
4. በማንበብ ልምዳቸው፡- ጥንቆላ' ምዋርት' መተት' አስማት... ጋር ተዛምዶ ያላቸውን መጻሕፍት ማንበብ ያዘወትራሉ፡፡
5. *<u>እንግዳ ቃላትን (ቋንቋዎችን) በመጠቀማቸው፡-</u>* አስነዋሪ የሆኑ ወይም ትርጉማቸው ግልጽ ያልሆኑ አዳዲስ ባዕድ ቃላቶችን በመጠቀማቸው፡፡
6. ባሉ ጉዳዮች ላይ አዳዲስ አማራጭ ፍላጎቶቻቸውን በማንጸባረቅ፡- በአካባቢያዊም ሆነ በጾታ ጉዳዮች ላይ ፍጹም ጽንፈኝነት' ከቤተ ሰብ ወይም ከማኅበረሰቡ ራሳቸውን በማግለል' ነውጠኝነት' ወዘተ...

- በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች በተናጠል ሳይሆን በአንድ ላይ በመሰባሰብ ችግሮቹ የሚገኙባቸውን ሊጠቁሙን ይችላሉ፡፡

# *የሚከተሉትን እናስተውል!!!*

1. ልናመልከውና ልንገዛለት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነና ይህንንም አጋንንት ራሳቸውም እንደሚያምኑ፡፡
   - *እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።; ያዕቆብ 2 ፡ 19፡፡
2. የግብጽ አስማተኞችም እግዚአብሑር በሙሴ እጅ ካደረጋቸው ተአምራት ጥቂቶቹን ብቻ ማስመሰል ቢችሉም በኋላ ግን አልሳካ ሲላቸው በሰይጣናዊ ምትሐት ላይ እግዚአብሔር ያለውን ኃይል በመቀበል *ጠንቋዮችም ፈርዖንን፡- ይህስ የእግዚአብሔር ጣት ነው አሉት የፈርዖን ልብ ግን ጸና፥ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ አልሰማቸውም።; ዘጸአት 8 ፡ 19፡፡
   - *መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።።; ኤፌ 6፡12
3. እግዚአብሔር አምላካችን ሁሉን ቻይ መሆኑ በርሱም ከተደገፍን ድልን ሁሉ ሊሰጠን ይችላል፡፡
   - *እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ሰለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።።; ሉቃስ 10 ፡ 18 · 20፡፡
4. የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡ ውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ከሆኑ ሐሰተኞች መምህራን ተጠበቁ፡፡ እነዚህ የእግዚአብሔርን ልጆች በስህተት ጎዳና ለመምራትና ለማጥፋት ይጥራሉ፡፡ ማቴዎስ 7 ፡ 15፡፡
5. ጉዳቱን ሳናውቅ ወይም ሳንረዳ ቀርተን በአዲስ ትምህርት ወይም ክህደት እንዳንወሰድ ዘወትር የተጠበቅን የተጠነቀቅን እንሁን፡፡ ገላትያ 1 ፡ 6 · 9፡፡
6. ሳንጠቀምበት ቀርተን ካልሆነ በቀር በዚህ የስህተት ጎዳና በመጓዝ የተገኙ ካህናትም ሆኑ ምዕመናን የሚታረሙበት ካልሆነም የሚለዩበት ሥርዓት (ሕግ) በቤተ ክርስቲያናችን ያለን መሆኑን እንወቅ፡፡

# ምን እናድርግ?

እኛ ወይም የምናውቃቸው እስካሁን በተመለከትናቸው ሐሰተኛ መንገዶችና ልምዶች ተሳትፎ አድርገን ወይም አድርገው ከሆነ፡•

1. ወደ ጥፋት በሚያደርሰን አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንደሆንን ወይም እንደሆኑ እንወቅ፡፡

2. ከንስሐ አባቶቻችን ጋር በመነጋገር ወደ እግዚአብሔር መንገድ እንዴት እንደምንመለስ እንረዳና እንመለስ፡፡

3. ወደዚህ የጥፋት ጎዳና ከመሯችሁ ሰዎች ጋር ያላችሁን ግኑኝነት አቋርጡ፤ ከነርሱ ጋር ሆነን ከእጃችን የገቡ ቁሳቁሶችም ካሉ እናቃጥላቸው፡፡

4. ወደ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በመመለስ ውበትዋን ትምህርትዋንና ሥርዓትዋን መርምረን እንወቅ፡፡

5. በቤተ ክርስቲያን በበለጠ ንቃትና ትጋት በመገኘት ሌሎችም በተመሳሳይ ወጥመድ እንዳይወድቁ እናስጠንቅቃቸው፡፡

*አምላካችን በቸርነቱ በእመቤታችን ምልጃ ቤተ ክርስቲያናችንንና ልጆችዋን ሁሉ ከክፉ ሁሉ ይጠብቅልን፡፡*

ወስብሐት

ለእግዚአብሔር፡፡